# የእግዚአብሔር ዝምታ እስከመቼ?

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ደንብ እና ሥርዓት
የተዘጋጀ

አዘጋጅ መምህር አንድነት አሸናፊ (B.Th)

የስነ መለኮት ምሩቅ

በ 2001 በድጋሚ ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights Reserved

## ምስጋና

በመጀመሪያ የተሰበረውን በሚጠግነው የመከራን ሸለቆ አቋርጠን እንድናልፍ ለሚያደርገው ለስም አጠራሩ ክብር ለሚገባው ለእግዚአብሔር ይሁን::

በመቀጠልም ይህ መጽሐፍ ተጀምሮ እስከሚያበቃ በምክር፣ በእርማትና አስፈላጊው ነገር ጊዜአቸውን ሰውተው ለረዱኝ ለቤተክርስቲያኒቱ ለሚኖሩት የቅድሥት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ምሩቃንና ደቀመዛሙርት፣ ለአባ አብርሃም ገ/ሚካኤል፣ ለወ/ት ትዕግስት በላይነህ ለመምህር ያሬድ ዮሐንስ፣ ለወ/ሮ ተናኜ ዜና ለወ/ሮ ፋንታዬ ያደታ፣ ለወ/ት ፍሬሕይወት ምገስ፣ ለአቶ ኪዳኔ እንዳሻው፣ ለአቶ ንጋቱ ኃ/ገብርኤል እግዚአብሔር ሰላሙንና ጸጋውን ያብዛልኝ እላለሁ::

## መታሰቢያነቱ

በሞት ለተለየኝ አባቴ ለአቶ አሸናፊ እና በሕይወት ላሉት ቤተሰቦቼ::

## ስጦታ

ከ____________________

ለ____________________

ቀን ____________________

# ማውጫ

**ምዕራፍ አንድ .......................................... 6**
እግዚአብሔር ማን ነው? .......................................... 6
ሀ. ሁሉን ቻይ ነው .......................................... 6
ለ. ሁሉን አዋቂ ነው .......................................... 7
ሐ. ፍቅር ነው .......................................... 7
መ. ጠቢብ ነው .......................................... 8
ሠ. መንፈስ ነው .......................................... 8
ረ. ብርሃን ነው .......................................... 9
ሰ. ቅዱስ ነው .......................................... 10
ሸ. ፍትሐዊ ነው .......................................... 10
ቀ. ዘለዓለማዊ ነው .......................................... 12

**ምዕራፍ ሁለት ..........................................**
የእግዚአብሔር ዝምታ .......................................... 13
ሀ. የማይናገሩ ሕፃናት ሲታረዱ .......................................... 13
ለ. ስራ በማጣት ስንንገላታ .......................................... 15
ሐ. ተርበን ባበላን፤ ጉድጓድ ውስጥ ስንጨመር .... 18
መ. ንጉሡ በወደደን ስንጠላ .......................................... 20
ሠ. ትዳራችን ፍቅር ሲያጣ .......................................... 22
ረ. መኖሪያችንን ጥለን ስንሰደድ .......................................... 24
ሰ. የድህነት ወላፈን ሲያቃጥለን .......................................... 26
ሸ. ያስታርቃሉ ያልናቸው ሲያጣሉ .......................................... 28
ቀ. ስርተን ያለ ደመወዝ ስንባረር .......................................... 30

www.ethiopianorthodox.org

በ. እስታውሱን ያልናቸው ሲረሱን........................32
ተ. መሞት አለባቸው ያልናቸው ሲኖሩ................33
ቸ. የተፈጥሮ አደጋዎች ሲያውኩን.......................36
ነ. መኖር አለባቸው ያልናቸው ሲሞቱ..................38

ምዕራፍ፡ ሶስት............................................40
ዝምታው እስከ መቼ?............................................40
ሀ. እግዚአብሔርነቱን እስክናውቅ ...........................41
ለ. የግፈኞች ጽዋው እስኪሞላ................................43
ሐ. ጠላቶቻችን ወዳጆቻችን እስኪሆኑ......................45
መ. እርሱ ለልጆቹ እስኪዋጋ ..............................46
ሠ. ዝም ያለበትን እስክናውቅ..................................47
ዋቢ. መጻሕፍት ........................................................48

# የእግዚአብሔር ዝምታ እስከመቼ?

## መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

በብልጽግናም ሆነ በድህነት፣ በደስታም ሆነ በሀዘን፣ በማግኘትም ሆነ በማጣት፣ ሀገረ ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የምንኖር ሰዎች የየራሳችን ጥያቄዎች አሉን። ጥያቄዎቻችን ከሰው አቅም በላይ ሲሆን የምናቀርበው ለእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር አቅም በላይ የሚሆን ጥያቄ የለምና።

ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር አሳልፈን የሰጠናቸው ነገሮችም ሆኑ ያቀረብናቸው ጥያቄዎች ቀናትንና ዓመታትን በመውለዳቸው ውስጣችንም የእግዚአብሔር ዝምታ እስከመቼ ነው? የሚል ሆኗል።

ይህንንም ጥያቄ መሠረት በማድረግ ይህንን መጽሐፍ አዘጋጀቻለሁ። የመጽሐፉ አንባቢ ብቻ ሳትሆኑ ተጠቃሚም ትሆኑ ዘንድ አሳስባለሁ።

መምህር እንድነት አሸናፊ



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ አንድ

*<u>እግዚአብሔር ማን ነው?</u>*

የእግዚአብሔርን ማንነት የዘመናት መለዋወጥ የማይቀይረው መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር ለሕዝቡ በውስጥዋም ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል" (መዝ. 86፣ 6) በማለት ስለሚነግረን የእግዚአብሔርን ማንነት የምናውቀው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ እግዚአብሔር እንዳለ ለማረጋገጥ አይሞክርም። የእግዚአብሔርን መኖር መሠረት አድርጎ ይጀምራል እንጂ እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረቱ ገልጿል። (ሮሜ 1፣ 19-21)

ሀ. <u>ሁሉን ቻይ ነው</u>

የሰውን ያህል የሚንቀሳቀሱ ነገሮችም ሆኑ እኛ ሰዎች ብዙ ነገር ማድረግ እንችላለን እንጂ ሁሉን ማድረግ አንችልም። ምንም ማድረግ አንችልም የምንል ሰዎች ቢያንስ አንድ ነገር ማድረግ እንችላለን። እንዲሁም ሁሉን ማድረግ እንችላለን የምንል ሰዎች ቢያንስ አንድ የሚያቅተን ነገር አለ።

ሁሉን ቻይ ነው ሲባል ሁሉን ታጋሽ ነው ማለትንም ያጠቃልላል። እግዚአብሔር ትዕግስተኛ ኃይሉም ታላቅ ነው" (ናሆም 1፣ 3) ይላልና። እኛ ሰውን ብንታገስ ወቅት፣ ቦታ ሰዓት አይተን ወይም ድጋሚ እስኪያጠፉ ጠብቀን አሊያም ሁኔታዎች





እስኪመቻቹልን ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ግን የሚታገሰው መታገስ የባሕርዮ ስለሆነ ነው።

ለ.<u>ሁሉን አዋቂ ነው</u>

የሰው አዋቂነት በመማር፣ በማየት፣ በልምድ ነው። ይህም ቢሆን ያለፈውን ነው የወደፊቱንም ቢሆን ገምተን እንጂ አይተን አይደለም ይህ ብቻ ሳይሆን የገመትነውም ላይሆን ይችላል።

የእግዚአብሔር አዋቂነት ግን ያለፈውን የአሁኑንና የወደፊቱን ነው። "አቤቱ አንተ እነሆ የቀድሞውንና የኋላውን አወቅህ" (መዝ 139፣ 1) እንዳለው ሁሉን አዋቂ ነው። አዋቂነቱ እንደሰው በመማር፣ በማየት በልምድ አይደለም።

የሰው አዋቂነት በተወሰኑ ነገሮች ላይ ነው። አዋቂ የምንላቸው ሰዎች እና እናውቃለን የምንል ሰዎች እንኳን የማናውቀው ነገረ አለ። እግዚአብሔር ግን ሁሉን አዋቂ ከመሆኑም በላይ እውቀቱ ጥልቅ ነው።

ሐ. <u>ፍቅር ነው</u>

ብዙዎቻችን በቤታችንም ሆነ በምንፈልገው ቦታ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" (1ኛ ዮሐ. 4፣ 8) የሚለውን ቃል እናደርገዋለን። እናት ልጇን ባል ሚስቱን ሌሎቻችንም የምንወደውን ነገር የምንወደው ለጥቅማችን ነው። የሚገርመው እግዚአብሔር እኛን መውደዱ ለራሱ ጥቅም አለመሆኑ ነው። የእኛ ፍቅር ለሰዎች በቃል ወይም ራስን በጠበቀ መልኩ በተግባር ሊሆን ይችላል የእግዚአብሔር ፍቅር ግን



www.ethiopianorthodox.org

ራሱን አሳልፎ ለክብሩ ባለመሳሳት ነው። "ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮሜ 5፣ 8)።

የሰው ፍቅር ገደብ አለው የእግዚአብሔር ፍቅር ግን ገደብ የለውም። ሰውንም የፈጠረው ካለው ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ ነው። ሲፈጥረንም በመልኩ ራሱን አስመስሎ ነው።

መ. <u>ጠቢብ ነው</u>

የእግዚአብሔር ጥበብ ለሠራው ሥራ፣ እየሰራ ባለውና ወደፊት በሚሰራው እየተገለፀ ነው። ለምሳሌ የፍጥረቱ ሥነ ስርዓት፤ ቀንና ሌሊት፣ ክረምትና በጋ፣ ያላቸው አካሄድና በተለይም ሰው ከጽንሰት ጀምሮ የሰውነታችን አካላት አፈጣጠራቸውና የተቀመጡበት ቦታ ጠቢብነቱን ያሳየናል።

በመዝ 103፣ 24 ላይ "አቤቱ ሥራህ እጅግ ብዙ ነው፣ ሁሉን በጥበብ አደረግህ" ብሏል። የሰው ጥበብ በመማርና በመመራመር ቢገኝ እንኳን ከሱ የተሻለ ጠቢብ ሲመጣ ጥበቡን ውድቅ ያደርግበታል። የእግዚአብሔር ግን መቼም አይወድቅም።

ሠ.<u>መንፈስ ነው</u>

እግዚአብሔር መንፈስ ነው ስንል የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ፣ የሚወሰን አካል የለውም ማለት ነው። በወንጌል "እግዚአብሔር መንፈስ ነው" (ዮሐ. 4፣ 24) ተብሎ ተጽፏል። እግዚአብሔር በአንድ





ቦታ ብቻ የሚወሰን አይደለም።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው ስንል በዓለም ሁሉ ሙሉ ነው የሌለበት ቦታ የለም ማለት ነው። "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ ወደሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ..." (መዝ. 138፣ 7) እግዚአብሔር በዓለም ሙሉ ነው በሁሉ ቦታ አለ ስንል በአንድ ጊዜ በሁሉ ቦታ መገኘት ይችላል ማለት ነው። ሰው በሁሉ ቦታ መገኘት ቢችልም በአንድ ጊዜ መገኘት አይችልም። ቅዱስ ጳውሎስም "ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም" በማለት በዓለም ሁሉ ሙሉ መሆኑን ተናግሯል። (ሐዋ. 17፣ 28) ።

ረ. <u>ብርሃን ነው</u>

ብርሃን ለመኖራችን ወሳኝ ነገር ነው። ያለብርሃን እፅዋት፣ እንስሳት፣ ሰውም መኖር አይችልም። ብርሃን ማለት የጨለማ አለመኖር ማለት ነው። እግዚአብሔር ብርሃን ነው ስንል ጨለማ በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም ማለት ነው። "እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም" (1ኛ ዮሐ. 1፣5) ይላልና።

በዚህ ዓለም ብርሃን የሆኑ ነገሮች ተለዋዋጭ ናቸው። ቀን በሌሊት ፀሀይ በጨረቃ ይለወጣሉ። ሰው የሰራው ብርሃንም ቢሆን በራሱ የመቆም ኃይል የለውም ፀሀይና ውሃን በመሳሰሉ ነገሮች ተደግፎ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔር ብርሃንነት ግን በምንም በምን ነገሮች ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን የባሕርዩ ነው።

ሰ. <u>ቅዱስ ነው</u>

ቅዱስ ነው ስንል ንጹሕ፣ ክፉት የሌለበት፣ የተለየ ማለታችን ነው። ሰዎችንም ሆነ ነገሮችን ቅዱስ ብለን ብንጠራም ቅድስና የባሕርያቸው አይደለም። ከንጉሡ ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ነው። እርሱ ግን ከማንም የተቀበለው ወይም እንደሰው በትጋት ያመጣው ሳይሆን የባሕርዩ ነው።

"እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" (ዘሌ. 19፣2) ተብሎ እንደተፃፈ እርሱ መቼም መች ቅዱስ ነው። እኛ ግን የምንሆን ነን።

የእግዚአብሔር ቅዱስነት እንደሰው በነገሮች መሳካት የመጣ ባለመሆኑ እንደሰው በነገሮች አለመሳካት የሚለዋወጥ አይደለም።

ሸ <u>ፍትሐዊ ነው</u>

ፍትሐዊነት የእግዚአብሔር አንዱ ባሕርይ ሲሆን ከፍቅር ብዙም አይለይም። ያ ፍቅር እውነተኛ ስለሆነ ፍትሐዊ ነው ማለት ነው። በመጽሐፈ ነህምያ 9፣ 33 ላይ "በደረሰብንም ነገር ሁሉ አንተ ጻድቅ ነህ አንተ እውነት አድርገሃልና" ተብሎ እንደተጻፈ።

ቅዱስ ጳውሎስም "እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና" (ሮሜ. 2፣11) ። በማለት ፍትሐዊነቱን ያስረዳል። ከብሉይ ኪዳን ነቢያት





የፍትሕ ባለድል የተባለው አሞጽ "ፍርድ እንደ ውኃ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ" (አሞፅ. 5፣24) በማለት ስለፍትሕ ገልጿል።

ፍትሕ በተፈጥሮው ማህበራዊ ነው። ስለዚህ ክርስቲያን ፍትሐዊ ሆነ ማለት ሌላው ተርቦ እሱ በልቶ ጠግቦ ተርፎት ይደፋል ማለት አይደለም። ያልለበሰን ሰው አይተን ካለን ላይ ማልበስ ፍትሐዊነት ነው። ፍትሕ የምንሰማው ሳይሆን የምንሰራው ነው።

እግዚአብሔር ፍትሐዊ ስለሆነ ኃጢአተኛውን ጻድቅ፣ ጻድቁን ኃጢአተኛ አይለውም። እኛም እንዲሁ እውነተኛውን እውነተኛ ሀሰተኛውን ሀሰተኛ ማለት አለብን እንጂ እንቅልፋሙን ትጉህ፣ ሌባውን መጽዋች፣ አጭበርባሪውን ታማኝ፣ ዘማዊውን ጻድቅ ማለት የለብንም።

እግዚአብሔር ፍትሐዊ ነው ሲባል መሀሪ አይደለም ማለት አይደለም። በፍትሐዊነቱ ውስጥ ምህረት አለ። መሀሪነቱ ፍትሕ አይለየውም ማለት ነው። "የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው ምሕረትና እውነት በፊትህ ይሄዳሉ" (መዝ. 88፣14) አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ፍትሐዊ ቢሆን ሰዎች ሲቸገሩ ለምን ያያል ይላሉ። ይህ የሆነው ከሰው ስህተት፣ ሊደረግ የሚገባው ነገር አለመደረጉ እንጂ እርሱ ፍትሐዊ ሳይሆን ቀርቶ አይደለም።



www.ethiopianorthodox.org

ቀ. <u>ዘለዓለማዊ ነው</u>

እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው ስንል መጀመሪያና መጨረሻ የለውም ማለት ነው። " አቤቱ አንተ ለትውልድ ሁሉ መጠጊያ ሆንህልን ተራሮች ሳይወለዱ ምድርም ዓለምም ሳይሰሩ ከዘለዓለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ" (መዝ. 89፣2) የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት ከሱ ውጭ ባለ ነገር ላይ የተመሠረተ አይደለም። የእኛ አኗኗር ግን በእርሱ ላይ የተመሠረተ ነው።

እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው ስንል አይለወጥም ማለትንም ያካትታል። ሰዎች ተለዋዋጮች መሆናችንን ነገሮችም ሆኑ ኑሮ ያሳየናል። ደስታና ሀዘን፣ እውነትና ሀሰት፣ ጽድቅና ኃጢአት፣ ማግኘትና ማጣት ይፈራረቁብናል። ይህም ብቻ ሳይሆን ለአንዱ ቸር ብንሆን ለሌላው ክፉ፣ ለአንዱ ታጋሽ ብንሆን ለሌላዋ ትዕቢተኛ ልንሆን እንችላለን። ቦታና ጊዜ አይተን እንለዋወጣለን።

እግዚአብሔር ግን "እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም" (ሚል. 3፣5) ብሏልና ጊዜ፣ ሁኔታ፣ ቦታ፣ ማንነትን አይቶ አይለወጥም። ትናንት ንጉሥ የነበረ ዛሬ ላይሆን፣ አምና ሠራተኛ የሆነ ዘንድሮ ላይሆን፣ አምና ባለትዳር የነበረች ዘንድሮ ላትሆን፣ አምና ሃይማኖተኛ የነበሩ ዘንድሮ ላይሆኑ፣ ትናንት ጥሩ የነበሩ ዛሬ ላይሆኑ፣ ዛሬ የሆኑትን የሆኑ ነገ የሚሆኑትን ላይሆኑ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን ከጊዜ በፊትም፣ በጊዜ ውስጥም፣ ከጊዜ በኋላም ቸርና ይቅርባይ፣ ፍቅር፣ መሀሪ፣





ዘለዓለማዊ፣ ጠቢብ፣ ሁሉን አዋቂ ወዘተ ነው። ምክንያቱም እርሱ በባሕርዩ ዘለዓለማዊ ነውና።

## ምዕራፍ ሁለት

<u>የእግዚአብሔር ዝምታ</u>

ከልባዊ መሻታችን ተነስተን ከራሳችን፣ ከትዳር አጋራችን ከልጆቻችን፣ ከወላጆቻችን፣ ከቤተሰባችን፣ ከዘመዶቻችን ከመንደራችን፣ ከሀገራችን፣ ከአህጉራችንና ከዓለማችን አንጻር እግዚአብሔር ዝም ብሏል ያልንባቸው ጉዳዮቻችን እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

ሀ. <u>የማይናገሩ ሕጻናት ሲታረዱ</u>

"ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው"(መዝ.126፣ 3) ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ልጆች በህጋዊም ሆነ ያለህጋዊ ጋብቻ ይገኙ ከእግዚአብሔር የተሰጡን ናቸው። ስለዚህ በጾታ ግንኙነት ወቅት እንደሚፀነሱ ሳናስብና ሳንዘጋጅ ከተፀነሱ በኋላ እንዲታረዱ ማቅረብ ነፍስ ማጥፋት ነው።

ጽንስን በማስወረድ ዙሪያ 3 ዓይነት ክርክሮች አሉ። እነዚህም

1. ጽንስ ስለማይናገርና ስለማይንቀሳቀስ ግማሽ ሰው ነው፤
2. ዛሬ ሰው አይደለም ነገር ግን ነገ ሰው ይሆናል፤
3. ፍጹም ሰው ነው

የሚሉት ናቸው ብዙ ሰዎች የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን



www.ethiopianorthodox.org

በመቀበል እናስወርዳለን ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ ፍጹም ሰው ነው ብለን ብናምንም በድፍረት እናስወርዳለን ይላሉ። ትክክለኛው ግን ባልና ሚስት ግንኙነት ካደረጉ ሰዓት ጀምሮ የተፀነሰው ፍጹም ሙሉ ሰው ነው። እኛ ያለን አካል በሙሉ አለው መጠኑ ይነስ እንጂ።

እግዚአብሔር ኤርሚያስን "በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ከማህፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ" (ኤር.1፣5) ብሎታል። ኤርሚያስን በማህፀን ሳለ ያወቀው ጌታ የእኛን ጽንሶችስ አያውቃቸው ይሆን? በደንብ ያውቃቸዋል። እባካችሁ እንኑር አታጥፉን ብለው መናገር ስለማይችሉ እንፈርድባቸዋለን። በሥላሴ አርአያ የተፈጠሩትንም በቢላ እንዲታረዱ እንወስናለን። እነሱም ጉልበትና አንደበት ስለሌላቸው ይታረዳሉ።

በዚህ ምክንያት የሚመጣ ችግር ሀሊናችንን እረፍት ይነሳዋል፤ ባለትዳሮችን ፍቅር ያሳጣል፤ ምድሪቱ የደም ጥላ ያጠላባታል።

ዓለማችን የህፃናትን ነፍስ መግደልን ህግ አድርጋ መቀበሏ የሚያጠራጥር አይደለም። በዚህ ዙሪያ ተጠያቂዎች የልጁ ነፍስ እንዲጠፋ የተስማማች እናት፣ የተስማማ አባት፣ ነፍስ አጥፊው የህክምና ባለሙያ፣ ያበረታታን፣ የመከርን፣ የገፋፋን፣ የደገፍን፣ ገንዘብ የሰጠን ሁሉ የኃጢአቱ ውጤት ገፈት ቀማሾች ነን።

ይህ ብቻ ሳይሆን በፍቅርና በእንክብካቤ ማሳደግ ሲገባን ወልደን ሜዳ የጣልን፣ ወልደን የካድን፣ በቁጣ በግፍ በድብደባ ራሳቸውን





ባራሳቸው እንዲያጠፉ ያደረግን ሁሉ ከተጠያቂነት አናመልጥም። በሀገራችን በኢትዮጵያ ብዙ ባይስፋፋም ለአቅመ ሔዋንና አዳም ያልደረሱትን ህጻናት ደም ለጣኦት አምላኪም ሆኑ ለጥንቆላ ማረድ ተመሳሳይ ነፍስ ማጥፋት ነው። ዛሬ ዛሬ አስፈንጥረው በማለት የህጻናት ነፍስ እንደስኘሪንግ የተቆጠረበት ጊዜ ነው።

ማንኛችንም ሰዎች በምንም ዓይነት እንወስን የሕጻናት ደም በከንቱ ሲፈስና ሕይወታቸው ሲያልፍ እንደዛ የምንሰስትላቸው፣ እስከናየቸው የምንናፍቃቸው፣ ለመምታት የምናዝንላቸው፣ ሲያለቅሱ የሚያስለቅሱንና ስናያቸው የሚያባቡን፣ ሲወድቁ የሚያባቡን ህጻናት ይጠፋሉ። እግዚአብሔር ዝም ያለ ቢመስለንም ዛሬ እየደነበርን መግፋት ያቃተንን መከራ የተሸከምነው የነሱ ውጤት ነው።

ታዲያ እግዚአብሔር ዝም ብሏል ማለት እንችል ይሆን? ዝም አላለም። ከዚህ የባሰ እንዳይመጣብን በንስሐ ተንበርክከን ይቅርታ እንጠይቅ አምላካችን የፍቅር አምላክ ነውና። እርሱ ጌታ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይታረቀን።

አሜን ይደረግልን

ለ. <u>ስራ በማጣት ስንንገላታ</u>

ብዙ ሰው ሥራ ማለት ጠዋት 2:30 ተገብቶ የሰዓት ፊርማ የሚፈርምበት 6:30 የሚወጣበት 7:30 ተገብቶ 11:30 የሚወጣበት በወር ደሞዝ የሚሰበስብበት ነው ብሎ ይተረጉማል።



www.ethiopianorthodox.org

የሥራ ትርጉም ግን ይህ ብቻ አይደለም።

ክርስቲያን ከኃጢአት በስተቀር ሙሉ ቀንም ይሁን ግማሽ ቀን ሰራን ሎተሪም ሸጥን፣ መደብ፣ ቢሮም ሰራን የፊልም ሥራ በላባችን ወዝ የሚከፈለን ክፍያ ሁሉ ሥራ ነው። ሰርቆ መብላት እንጂ ሰርቶ መብላት ኃጢአት አይደለም።

ብዙዎቻችን በተለይም በወጣትነት ዕድሜአችን ሥራን የማስታወቂያ ቦርድ ላይ ብቻ ስለምንፈልግ እኛ እንዳሰብነው ስላልተሳካ በመርጃ ጊዜአችን ተረጂ፣ በመጠሪያ ጊዜአችን ተጧሪ የልጅ ጡረተኞች ሆነናል።

አንዳንዶቻችን መማር የምንችልበት ገንዘብና አመቺ ሁኔታ እያለ በዛ ሳንጠቀም ቤተክርስቲያን መጥተን ምሬታችንን እናሰማለን። መጽሐፈ መክብብ ም. 3፣ 1-9 "... ለመስራትም ጊዜ አለው ለማልቀስ ጊዜ አለው..." ስላለ በጊዜአችን ልንጠቀምበት ይገባል።

ተማርን ከዚህ በኋላ ሥራ ነው የምንፈልገው ብለን አልተማሩም፣ ከእኛ በታች ናቸው ከእነሱ ይልቅ ሥራ የማግኘት እድን አለን ብለን ስንጠብቅ ዲግሪና ዲፕሎማችን በላብ በፀሐይና በዝናብ የተበላሸብን ብዙ ከመሆናችንም በላይ የምናቀርበው እጅ መንሻና ጉርሻ ባለመኖሩ ሳይመሽ የመሸብን ጥቂት አንባልም።

በመከራና በችግር ተጠብሰው በእግር እየሄዱ እኛን በመኪና ልከው፣ እነሱ ቆሎ ቆርጥመው ለእኛ እንጀራ እያበሉ ጠላ ሸጠውና





የቀን ሥራ ሰርተው ለወግ ለማዕረግ ያደረሱንን ወላጆቻችንን ሳንደርስላቸው ሞት ይቀድመናል።

ከዚህ ሁሉ መከራ ጋር ስንኖር ነው እግዚአብሔር ዝም ብሏል ለምን አያየኝም? ወይ ውረድ ወይ ፍረድ የምንለው።

ንጉሠ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ በጥብርያዶስ ባሕር ዳርቻ በበሽተኞች ላይ ያደረገውን ምልክቶች ስላዩ ብዙ ሕዝብ ተከትሎት ነበር። ፊልጶስን ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚሆን እንጀራ ከወዴት እንደሚገዙ ጠየቀው። ፊልጶስም የኢየሱስን ማንነት በራሱ ክንድ ገምቶ ትንሽ ትንሽ እንኳን እንዲቀበሉ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ አይበቃቸውም ብሎ መለሰ።

የእግዚአብሔር ማንነት በእኛ አቅም አይለካም። ይህንን ያልተገነዘበው እንድርያስም አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና እዚህ አለ። ነገር ግን እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆናል? አለ። ያ ትንሽ ብላቴና ቀኑ እየመሸ ቢሄድም የሚገዛው በትጋት እየፈለገ ነበር። ያንን ሸጦ የሚማር ይሆናል፣ የሚጦራቸው ቤተሰቦቹ ይኖሩ ይሆናል፣ ወላጅ የሌለው ብላቴና ይሆናል፣ ተበድሮ ባለዕዳ ይሆን ይሆናል። እርሱ ግን እየመሸ ቢሄድም ትጋት ላይ ነበርና ልፋቱ ዋጋ አገኘ። (ዮሐ. 6፣1-14)

እኛም ከስንፍና ይልቅ ለትጋት፣ ከሀሜት ይልቅ ለሥራ ዋጋ ብንሰጥ ውጤቱ እንደሚያምር ከዚህ እንማራለን። ሲጀመር የለፋንለት



www.ethiopianorthodox.org

ነገር ሲመሽ ትርፉ አስራ ሁለት መሶብ ይሆናል። ምክንያቱም የጌታ ኢየሱስ እጅ ይኖርበታልና።

እግዚአብሔር በሥራ ማጣታችን ዝም የሚለው ለኛ ሥራ መስጠት ተስኖት አይደለም። ምናልባት ከልባችን አልፈለግን ይሆናል፤ በትምህርት መረጃችን ተመክተን ይሆናል፤ ሥራውና ሠራተኞቹ ተራዎች ናቸው ብለን የናቅናቸው ካሉ ንቀታችን የትም እንደማያደርሰን ሊያሳየን ይሆናል፤የማንጠቀምበት ሆኖ የተሻለ ሊሰጠን ይሆናል፤ ወንጀል የሚሰራበትም ቦታ ከሆነ ሊሰውረን ይሆናል፤ የምንገባበት ቦታ ያሉትም ሰዎች ግፈኞች ከሆኑ የግፍ ጽዋቸው እስኪሞላ ይሆናል።

በጽናት በሰው ላይ ተንኰል ባለመስራት በህሊና ሰላም ተጉዘን የምንፈልገውን ያገኘን ዕለት አላቸው ከምንላቸው በላይ ያደርገናል። "ጌጣ መለወጥ ባንችልም ባዶ እግራችንን አይደለንም፤ ልብስ ቅያሪ በብዛት ባይኖረንም እራቁታችንን አይደለንም፤ መርጠን እንብላ እንጂ የምንበላው አላጣንም፤ የተመቻቸ ቤት አይኑረን እንጂ ማደሪያ አላጣንም ለነገ አናሳድር እንጂ ለዛሬ አላጣንም። " ወደ ዓለም ምንም አላመጣንምና እንዳችም ልንወስድ አይቻለንም ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል" (1ኛ ጢሞ 6፤9)

ሐ. <u>ተርበን ባበላን፤ ጉድጓድ ውስጥ ስንጨመር</u>

የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ምግብ ሊያደርስ ወደ በረሃ





ሲጓዝ የእርሱ ምግብ አልቆ የወንድሞቹ ብቻ እጁ ላይ ቀርቶ ነበር። ዮሴፍ ግን ለወንድሞቹ ረሀብ አደርስላቸዋለሁ ብሎ ሶስት ቀን በረሀብ ቆይቶ በሶስተኛው ቀን ረሀቡ ስለከበደው በዛፍ ስር ተቀምጦ ያለቅስ ጀመር። የጌታ መልአክ ጐልማሳ ሰው መስሎ ተገልጦለት ምን ያስለቅስሀል? ሲለው ራበኝ፣ ጠማኝ አለው። ከያዝከው ለምን አትበላም? አለው ይህማ አባቴ ለወንድሞቼ ስጥ አለኝ እንጂ አንተ ብላ አላለኝም አለው። (ዘፍ. 37፤ 1-17)

መልአኩም የአባትን ፈቃድ ካከበሩ ድንጋይ ዳቦ ይሆናል ብሎ ድንጋዩን ዳቦ አድርጐለት ተመግቧል። ቸርነት፣ በጐነት፣ ቅንነት፣ ለሌላው ማሰብ ላለን ሰዎች አይበላም አይጠቅምም የተባለውን ድንጋይ ወደ ዳቦነት መቀየር እግዚአብሔር ይቻለዋል።

ክፋት ተንኰል፣ ምቀኝነት ያለን ሰዎች ደግሞ እንኳን ድንጋይ ዳቦ ሊሆንልን፤ ዳቦው ወደድንጋይነት ይለወጥብናል። የምንበላው አጥተን እንዳልተቸገርን የምንበላው ሲገኝ ጐተራ ሞልተን፣ ቤታችን ተትረፍርፎ መብላት አቅቶን ካሮት ቆርጥመን እናድራለን።

የጌታ መልአክም ወንድሞቹ ያሉበትን ቦታ ስለነገረው ወደ ዶታይን ጉዞ ጀመረ። ሲቀርብም ወንድሞቹን ከሩቅ አይቶ ደስ አለው። ተርቦ ያመጣውን ሊበሉለት ነው ተጠምቶ ያመጣውን ሲጠጡ አይቶ በደስታቸው ደስ ሊሰኝ ነው።

ተርቦ ምግብ ያመጣላቸው ዮሴፍም ሲቀርባቸው ምግቡን ተቀብለው ልብሱን ገፍፈው ውኃ በሌለበት ደረቅ ጉድጓድ ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

ማሉት። ዮሴፍ ግን ጉዞው ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበር እንደነሱ ሃሳብ አልተጕዳም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ ክርስቲያን የማይኖርበት ሀገርና የማይስማማው ኑሮ የለም።

የተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ ባንገባም የጉድጓድን ያህል መውጫው የከበደ መከራና ችግር ውስጥ የከተቱንን ሰዎች እያየን ይሞታሉ ስልን ሲኖሩ፣ ነገ ሞታቸውን ስንጠብቅ ተነገ ወዲያ ህይወታቸውን እናያለን። በዚህ ጊዜ ተርበን ባበላን ተጠምተን ባጠጣን ታርዘን ባለበስን ተቸግረን መፍትሔ ባስገኘንላቸው ጉድጓድ ውስጥ ስንጨመር እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? እንላለን።

እግዚአብሔር ሰዎቹ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ ሊያሳይ፣ ነገ በእነሱ ላይ የበላይ ሊያደርግ ፈልጎ፣ የዘራነው የኃጢአት ዘር ቢኖር የምናጭደው መከራ እንዲሆን ዛሬ ወደ ጉድጓዱ ስንገባ ዝም ቢልም ነገ ደረጃ ላይ ሊያወጣን ይሆናል። ከነዚህም ሌላ እግዚአብሔር የሚያውቀው እኛ የማናውቀው ምክንያት አለ። የእግዚአብሔርን ሃሳብ ያውቅ ዘንድ ማን ይችላል? ማንም።

እግዚአብሔር አብሮን ጉድጓድ ውስጥ ይገባል። ያለ እግዚአብሔር ሜዳ ላይ ከመሆን ከእርሱ ጋር ጉድጓድ ውስጥ መሆን ይበልጣልና።

አሜን ይደረግልን።

መ. <u>ንጉሡ በወደደን ስንጠላ</u>

ሜዶናዊው ዳርዮስ በመንግስቱ ላይ ይሾማቸው ዘንድ ከወደዳቸው





ሶስት ሰዎች አንዱ ነቢዩ ዳንኤል ነበር። ዳንኤልም መልካም መንፈስ ስላለው ከአለቆችና ከመሳፍንት በለጠ ንጉሡም በመንግስቱ ላይ ይሾመው ዘንድ አሰበ (ዳን.6፣ 1-28)

የዚያን ጊዜም አለቆችና መሳፍንቱ ስለመንግሥቱ በዳንኤል ላይ ሰበብ ይፈልጉ ነበር ነገር ግን የታመነ ነበረና ስሕተትና በደልም አልተገኘበትምና በእርሱ ላይ ሰበብና በደል ያገኙበት ዘንድ አልቻሉም።

የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ የዕውቀቱን ሽታ በገለጠልን፣ እርሱ በጠገነን፣ ቁስላችንን በፈወሰው፣ ደዌአችንን ባራቀው፣ ምስጋናችንን በተቀበለው የሚጠሉን አሉ።

ስትሰብኩ ድምጻችሁ አስጠላን፣ ስትዘምሩ ወዝ የለውም፣ ስትቀድሱ አይመስጥም፣ ስታገለግሉ አንረካም፣ ምስጋናችሁ በዛ፣ ጥቅሳችሁ ከመጽሐፍ ቅዱስ የለም፣ ድምጽ ማጉያችሁ ጮኸብን የሚሉ አሉ። በአጠቃላይ ውሃ ቀጠነ ፈደል ተጣመመ በማለት ንጉሡ እግዚአብሔር በወደደን የሚጠሉን አሉ።

ይህ ጥላቻቸው እርምጃውን ሲጨምርም ዳንኤልን ከአምላኩ ሕግ በቀር ሰበብ አናገኝም ብለው ዳንኤልን ለማጥመድ ሰው ሰውኛ ውሳኔ አስወሰኑ። ዳንኤልም ለአምላኩ ሲገዛ በመገኘቱ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ተርበው በከረሙ አንበሶች ጉድጓድ ተጣለ።

ዛሬም ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገራችን ያስጠላቸው፣



www.ethiopianorthodox.org

ስብከታችን የኃጢአታቸውን ሰንኮፍ በፈቀፈቀው፣ ዝማሬአችን የውሸታቸውን ንግግር በፈታው፣ ቅዳሴአችን የተንኰል ሕሊናቸውን በፈታው የሚጠሉን አሉ።

ይህንን በማሰብ መንፈሳዊነታችንን ለመተው ክርስትና ያስጠላን፣ ልብሳችንን የሰበሰብን፣ በመንፈሳዊነታችን ምትክ ሥጋዊ፣ በመጸወትነው ምትክ ልንሰርቅ፣ በታገስነው ምትክ ትዕቢተኞች ልንሆን፣ በቆምነው ምትክ ልንተኛ፣ በተቀደስነው ምትክ ልንረክስ የተዘጋጀን አለን። ለምን? ቢባል እግዚአብሔር ዝም ብሏልና።

እግዚአብሔር ዝም ያለ፤ ጥላቻቸው የበዛ ይምሰለን እንጂ "በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን"

(ሮሜ. 8፣37)

የወደደን ጌታ ምስጋና ይድረሰው።

አሜን።

ሠ. <u>ትዳራችን ፍቅር ሲያጣ</u>

ሰዎች በምድር ላይ ከሚኖሩበት ሁለት ዓይነት አኗኗር አንዱ በጋብቻ ሕይወት መኖር ነው። በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ዛሬ የትዳር ሕይወት ውስጥ እንኖራለን።

የትዳር ሕይወታችን ግን እኛ እንዳሰብነውና እንደጠበቅነው አልሆነልንም። ባል ወጥቶ ወርዶ፣ ለፍቶ ተግቶ፣ ቀንና ሌሊት፣ሰኞና ማክሰኞን መለየት እስኪከብደው ሠርቶ ያመጣውን ገንዘብ





ለሚወዳትና ለሚያምናት ሚስቱ ከወር ታደርሳለች ከኔ ትሻላለች ብሎ ይሰጣታል።

እርሷ ግን ታለማለች ሲባል አጥፍታ፣ ትቆጥባለች ሲባል አባክና፣ ለፍሬ ታበቃለች ሲባል ገለባ ታደርገዋለች። የሚያሳዝነው አልበቃ አልደርስላት ብሎ ቢሆን መልካም ሲቻል ማበላሸትና ሆን ብሎ ማባከን ግን ባልን ከማሳዘኑም በላይ እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? ያስብለናል።

ሚስት ጥሩ፣ ጨዋ፣ ሥራውን አክባሪ፣ ቤተሰቡን ወዳጅ፣ ሚስቱን አፍቃሪ፣ ለልጆቹ አዛኝ ባል አለኝ በጊዜ ይገባል ብላ ትጠብቃለች። እንደተጠበቀው ያልሆነው ባል ግን ካለው በገንዘቡ ከሌለው ተበድሮ ጠጥቶ መምጣቱ ሳያንስ ሰክሮ ከተኙ በኋላ ይመጣል። የመጣው ሌሊት በመሆኑ መከረኛዋ ሚስት ተነስታ በር ብትከፍትም የሚጨመርላት ዱላና ድብደባ ይሆናል። የተኙ ሕጻናት ተነስተው እየተደበደቡ ካልሆነም እየተሰደቡ ጐረቤትና ጐዳና ይወጣሉ። ቢመከር አይሰማም ቢነገረው ማን አለብኝ ይላል። ሚስት ይህንን ስታይ ከማልቀሷም በላይ እግዚአብሔር የለምን? ዝምታው እስከመቼ? ትላለች።

የሥራው ሁኔታ ከብዙ ሰዎች ጋር የማያገናኘው ባል ሀገር ሰላም ነው ቤቴ ገነት ነው ብሎ ከዋለበት የሥራ ቦታ ሚስቴ ልጆቼ ብሎ ቤቱ ይገባል። የሥራውን ሁኔታ ያልተረዳች ሚስት እንዴት ከነእገሌና ከነእገሊት ጋር አየሁህ፣ ለምን በዛ መንገድ አለፍክ፣ እንዴት እስካሁን ይቆያል ትላለች። ይህም አልበቃት ብሎ በመንደር ውሻ



www.ethiopianorthodox.org

በጐረቤት ዶሮ እያመካኘች የስድቡን ናዳ የድንጋይ ቁልል ያህል ትከምረዋለች። ይህ የከበደው ባል መቼ ነው ጌታ ከዚህ ኑሮ የሚገላግለኝ? በማለት የጌታን ዝምታ ይወቅሳል።

ለባሏ ታማኝ ለልጆቿ ፍቅር የሆነች ከክፋትና ከነገር ርቃ ለብልጭልጩ ዓለም ሳትገዛ ቤቴ ትዳሬ ብላ ትኖራለች። ባል ሚስቱን አካሉን ትቶ ከሌላ ሴት ጋር ሲዘሙት ይማራል የመለሳል ብላ ትጠብቀዋለች። ትዕግስቷ ፍሬቿ የመሰለው ባል በዚህ ድርጊቱ ሲገፋበት በንስሐ አባቷ በሥራ ባልደረቦቹ ብታስመክረውም አልሰማ ይላል።

በዚህ ምክንያት ትዳር የሳይኮሎጂ ምሁራን፣ የሥነ ልቦና ጠበብት ቢለፉለት የንሰሐ አባት ቢመክር ትዳር አልሆን ሲል ፍቅር በጥላቻ ይተካል። የዚህን ውጤት የዓመታቱን መርዘም በማየት የምናመሰግነውን ጌታ ከማመስገን ይልቅ እናዝንበታለን። ምላሹም ይፈጥን ዘንድ ምነው ዘገየ እንለዋለን።

ያደፈው ኑሯችን እስኪጸዳ፣ የመከርነው ምክር እስኪሠራ፣ መታገሣችን ውጤት እስኪያመጣ እንጠብቃለን። ነገም ሌላ ቀን ነውና "በለሷን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል" ይላልና ጌታ።

ጌታ መልካሙን ፍሬ ያብላን።

አሜን።

ረ. <u>መኖሪያችንን ጥለን ስንሰደድ</u>

ክርስቲያኖች መኖሪያችን በሰማይ ቢሆንም ለምድራዊ





ሕይወታችን መኖሪያ አያስፈልገንም አንልም። ቤታችን፣ ሰፈራችን፣ ሀገራችን ብለን ኑሯችንን እንኖራለን። ኑሮዬ ብለን የያዝነውን ኑሮ ስንኖር የመኖራችን ሁኔታ ብንገፋው የማይገፋ፣ የማይሳካ ይሆንብናል።

ውለን ማደር፣ ሠርተን መግባት ብንችልም ኑሯችን ከእጅ ወደ አፍ ይሆናል። ዛሬን መኖር ብንችልም ነገ ግን ያስፈራናል። ስለዚህ የተሻለ ኑሮና ሥራ ፍለጋ እንሰደዳለን።

ለመኖር በምናደርገው ውጣ ውረድ ውስጥ መኖራችን ያላስደሰታቸው ሰዎች መከራ ያደርሱብናል። ከአባትና ከእናቱ ቤት ለወንድሞቹ ምግብ ሊያደርስ የሄደው ዮሴፍ የምድያም ነጋዴዎች ሲያልፉ ወንድሞቹ ዮሴፍን አንስተው ከጉድጓድ አወጡት ለእስማኤላውያንም ዮሴፍን በሃያ ብር ሸጡት እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት። (ዘፍ. 37፣ 28)

ከእርሱ መንገድኑት የተማሩ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ከያዙ ወደየትም ይሰደዳሉ። ቤታችን መንደራችን ሀገራችን መኖሪያችን ካልንበት ወደንም ሳንወድም እንሰደዳለን። ወላጆቻችን እየናፈቁን በሰው ሀገር ልጆቻችን እንጀታችንን እየበሉን የሀሳብ አለንጋ ሲገርፈን፣ ፍቅረኞቻችን ከዛሬ ነገ ይመጣሉ ሲሉን ነገ የማንደርስበት ሲሆን ለወንድም እህቶቻችን ከዛሬ ነገ እንደርስላቸዋለን ስንል መከራውን ገፈት ጠጥተው ሞት ሲቀድማቸው ልባችን ይደማል።

የሰራነው ቤታችንን፣ የወለድናቸው ልጆቻችንን፣



www.ethiopianorthodox.org

የወለዱን ወላጆቻችንን ጥለን እንሰደዳለን። ይህ ብቻ ሳይሆን የምንበላው ስናጣም በረሃብ ምክንያት መኖሪያቸውን ቤተልሔምን ጥለው ወደ ሞአብ ምድር እንደተሰደዱት አቤሜሌክ፣ ኑሃሚንና ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው እንሰደዳለን። (መጽ.ሩት1፣ 1-መጨረሻው)

እነዚህን መከራዎችና የመፍትሔውን መዘግየት ስንመለከት እግዚአብሔር መመልከት ትቷል፣ ቢያይም ዝም ነው የሚለው ትቶኛል በማለት ተስፋ እንቆርጣለን። "ስምህን የሚያውቁ ሁሉ በአንተ ይታመናሉ አቤቱ የሚሹህን አትተዋቸውምና" (መዝ. 9፣10) ይላልና አይተወንም።

ሰ. <u>የድህነት ወላፈን ሲያቃጥለን</u>

ክርስትና ደሀ እንድንሆን አትሰብክም፤ ደሀ መሆንም ለመንግስተ እግዚአብሔር መስፈርት አይደለም። ብዙዎቻችን ግን ድሆች ነን። ያልተማርነው ትምህርት፣ ያልሠራነው ሥራ፣ ያልወጣነው ዳገት፣ ያልወረድነው ቁልቁለት የለም። ደሀ ማለት እንደሀገሩ ይለያያል። የአሜሪካ ደሀ የኢትዮጵያ ሀብታም ሊባል ይችላል።

ደሀ ከመሆን መቼ እንደምንላቀቅ ስናስበው ደሀ ሆነን እንድንኖር የተፈረደብን ይመስለናል። ድህነት ከእግዚአብሔር የመጣ አይደለም።

ገንዘብ አጥተን የምንበላው፣ የምንጠጣው፣ የምንለብሰው፣ ማጣት የገንዘብ ድህነት ነው። ጥሩ ማሰብ፣ መልካም መሆን፣ ጥሩ መስራት፣ ስናጣ መንፈሳዊ ድህነት ነው። በገንዘባችን ጠጥተን ስንሰክር የሞራል





ድህነት ነው። በማወቅ መቆጠብና መጠንቀቅ ሲገባን ባለማወቅ ስናጠፋ የዕውቀት ድህነት ነው።

እኛ ተርበን በምግብ የሚጫወቱ ሰዎች ስናይ፣ ልብሳችን እላያችን ላይ አልቆ ዛሬ የለበሱትን ነገ የማይደግሙትን ስንመለከት፣ በእግር መሄድ ደክሞን ስንቀመጥ አጠገባችን የተቀመጡ በመኪና መሄድ ሰልችቶኝ ነው ማለታቸውን እንሰማለን። ትላልቅ ብሮችን በስም እንጂ በመልክ የማናውቃቸውን ያህል ኪሳችን ውስጥ ያሉትን ጥቃቅን ብሮችና ሳንቲሞች በስም እንጂ በመልክ የረሱ ሰዎች እንዳሉ ስናይ።

እግዚአብሔር ሀብታሞችን የፈጠረው ድሆችን እንዲረዱ ነው የሚለውን ተረት ተረት ስንሰማ፣ ያቅፉናል ብለን ስንጠብቅ ውሻ ታቅፈው ስናያቸው፣ ጥሩ ምግብ ይሰጡናል ስንል የሻገተ ሲሰጡን አካፈሉን ስንል ፍርፋሪ ሲሰጡን፣ እግዚአብሔር ፈጥሮ እንደተወን፣ አይቶን እንደረሳን እንቆጥራለን።

ያለንን ማካፈል እንጂ ፍርፋሪ መስጠት ክርስትና አይደለም ጌታ "ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" (ማቴ. 7፣13) ነው ያለው።

የልብስ ደሀ የሆንነው ልብስ ጠፍቶ ሳይሆን ዛሬ ለብሰው ነገን የማይደግሙት ልብስ፤ ለሌላቸው መድረስ ስላልቻለ ነው። የምግብ ደሀ የሆንነው የምርት ማነስ ገጥሞን ሳይሆን ተርፎ የሚሻግተውና የሚጣለው ምግብ ለተራብነው መድረስ ስላልቻለ ነው። የገንዘብ



www.ethiopianorthodox.org

ደሀ የሆንነው በዓለም ያለው ብር አልቆ ሳይሆን ብራችንን ማስቀመጫና የት እንደምናረገው የቸገረን ሰዎች ገንዘብ የሌላቸውን ስላላሰብን ነው።

በአጠቃላይ ደሀ የመሆናችንን ነገር ስናስበው እግዚአብሔር ድሀ ለመሆናችን አስተዋጽኦ ያደረገ ይመስለንና በዝምታው እንባችን ይፈሳል። እንባችንንም አላብሰው አለ እንላለን። የዓለማችን ችግር የማስተዳደር እንጂ የቁስ አካል አይደለም።

በድህነት ወላፈን ስንገረፍ ከዚህ ነፃ ለመውጣት አስተዋጽኦቸው መፈለጉን የረሱ ሰዎችን ጌታ ያስታውስልን።

አሜን

ሽ. <u>ያስታርቃሉ ያልናቸው ሲያጣሉ</u>

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና" (ማቴ. 5፣ 9) ብሎ አስተምሯል። ማስታረቅ የእግዚአብሔር ልጅ ያስብላል። የእግዚአብሔር ልጆች የሚያስታርቁት ማስታረቅ የእግዚአብሔር ልጆች ጠባይ ስለሆነ ነው። ከሰዎች ጋር የምንጣላው የመጣላት ዓላማ ኖሮን አይደለም። የሁላችንም አስተዳደግና የመረዳት ችሎታ አንድ ዓይነት ባለመሆኑ አለመግባባት ይፈጠራል። እነዚህ አለመግባባቶች ሲያድጉ ወደ ቃላት ጦርነት ከዚያም ወደመደባደብ ያደርሳሉ።

በዚህ ምክንያት በወላጆችና በልጆች መካከል የሚፈጠር ግጭት የእስራኤልና የፍልስጥኤም ያህል የደፈጣ ውጊያ ይሆናል። ይህንን





ጉዳይ ይፈታሉ ያልናቸው አስታራቂዎች በወላጆችና በልጆች መካከል ገብተው አባታችሁ ከእናንተ ሌላ ልጆች አለው፣ ልጆቻችሁ ቤታችሁን ሊያፈርሱ ተዘጋጅተዋል በማለት በእሳት ላይ ቤንዚን የማርከፍከፍ ያህል ነገሩን ያባብሱታል።

ባልና ሚስት ባል ሲቆጣ ሚስት ታግሳ፣ ሚስት ስትናገር ባል ታግሶ ተቻችለው መኖር ይገባቸዋል። እንዲህ አልሆን ብሎ በከባዱም ችግር በውሀ ቀጠነውም ችግር ቤታቸው ትንሽ ጦርሜዳ ይሆናል። ይህንን ለመፍታት በሀገር ሽማግሌነታቸው የእድሜ ካባ የደረቡ የሽበት አክሊል የደፉ አረጋውያን ፈልገን አስታርቁልን ብለን ኃላፊነት እንሰጣለን፤ መልካሙን ውጤት ለመስማት ስንጠባበቅ ገና ከጅምሩ በቀን ስንት ተከፍላላችሁ? ይላሉ። ዋጋውን ተስማምተን ውጤቱን ስናይ ያስታርቃሉ ያልናቸው ሲያደባድቡ፣ ያስማማሉ ያልናቸው ሲያናክሱ፣ ይቻቻላሉ ያልናቸው ሆድ ሲብሳቸው፣ አብረው ይኖራሉ ስንል ንብረት ሲከፋፈሉ እናያለን።

ያስታርቃሉ ያልናቸው ሰዎች በማጣላታቸው አረጋውያን ያለጧሪ ሲቀሩ ህፃናት ለጐዳና ተዳዳሪነት፣ ወጣቶች ለሴተኛ አዳሪነት ሲዳረጉ በማየታችን አለመፈጠርን የተመኘን ብዙዎች ነን።

በአንድ የሥራ ቦታ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በመልክ፣ በአስተሳሰብ የተለያየን ብንሆንም ኑሮን ለማሸነፍ ላይ ታች ስንል በመካከላችን በተፈጠረ አለመግባባት ያስታርቃሉ ያስማማሉ ብለን ሰው መርጠን ቀን ወስነን እንለያያለን። ቀኑ ሲደርስ መልካም የምሥራች



www.ethiopianorthodox.org

ስንጠብቅ ፋይልህን አጠፋ፣ መረጃህን አበላሸ በማለት መፍትሔ ስንጠብቅ ችግር የሚያስወልዱ ሰዎች ሲገጥሙንና የሥራ በታችን ነገን መኖር የሚያስፈራን ሲመስለን እንጨነቃለን። ይህንን በማየት እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? እንላለን።

ቀ. <u>ሰርተን ያለደመወዝ ስንባረር</u>

ለመኖር መሥራት የግድ በመሆኑ እንሰራለን። የሰራንበትን ዋጋ ማግኘት ግን ለአንዳንዶቻችን አስቸጋሪ እየሆነ ነው። በተለይም በቤት ውስጥ ሠራተኝነት የምንተዳደር ሰዎች የየዕለት ኑሮአችን የሰቀቀን ኑሮ ነው ቢባል ማጋነን አይደለም።

የአሰሪዎቻችን ልጆች ምግብ በልተው እየተረፋቸው እኛ ቀምሰን የጾም ያህል ስናድር፣ የልብሱን ብዛት በማናውቀው ቤት ውስጥ እየሰራን የለበስነው ልብስ ተቀዳዶ በብርድ አለንጋ ስንገረፍ አንጀታችን ይቃጠላል። ሕጻናትን ትምህርት ቤት እያደረስን አቅሙ ስለሌለን ሲማሩ እያየን የትምህርት ቤት በር እያየን በቀን የመሸብን ጥቂት አንባልም።

"እነርሱ ግን በጣታቸው እንኳን ሊነኩት አይወዱም" (ማቴ. 23፣ 4) እንደተባለው ሊነኩት እንኳን የማይወዱትን ሥራ ቤተክርስቲያን ለቅዳሴ ሲሄዱ የሚቆዩት ሶስት ሰዓት ያህል ሲሆን እነርሱ ግን በግማሽ ቀንም ሊያልቅ የማይችል ሥራ ይሰጡናል። ሲመለሱም እንዴት እስካሁን አላለቀም በማለት ስድብ፣ ድብደባ





ማንገላታት፣ ንቀት የዕለት ምግባችን ይሆንብናል።

አሰሪዎቻችን እንደዚህ እየደረጉ የሚጸልዩትን ጸሎት እግዚአብሔር ፍትሐዊው አምላክ ይሰማ ይሆን? "ስለምን ጾምን? አንተም አልተመለከትኸንም? ሰውነታችንንስ ስለምን አዋረድን አንተም አላወቅህም? ይላሉ። እነሆ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ... እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን?" (ኢሳ. 58፣1-10) በማለት ሠራተኞችን በማስጨነት የሚጾም ጾም ውጤቱ አለመሰማት መሆኑን ይናገራል።

የሚያሳዝነው ይህ ብቻ ሳይሆን አብዛኞቻችን ሠራተኞች ደመወዛችንን የምናስቀምጠው አሰሪዎቻችን ጋ በመሆኑ ሊያባርሩን ሲፈልጉ በውሃ ቀጠነ ትዕዛዝ በእቃ ሰበራችሁ ሰበብ ደመወዛችሁ ለጠፋው ዋጋት ይውላል በማለት ያለደመወዝ ባልጠበቅነው ቀንና ሰዓት ያውም ከድብደባ ጋር እንባረራለን።

ዛሬስ ቢሆን በአሰሪዎቻቸው እንደፈርም፤ እኛ ሠራተኞች ነን፣ የኑሮ መከራ ከብዶናል፣ ቤተሰብ፣ ልጅ፣ ትዳር በሽታ አለ ብለን ለህሊና በሚከብደው ለማውራት በሚሰቀጥጠው ኃጢአት ስላልተባበርን ከሥራ የተባረርን ልጆቻችንን መመገብ ያቃተን የምንሰራበትን ቤት መቀየየር የሰለቸን የለንም ይሆን? በእግዚአብሔርስ ያለን እምነት ሙሉ ይሆን? አይቆናል ብለንስ እናምናለን? ዘገየብን ከማለት በስተቀር?



www.ethiopianorthodox.org

በ. <u>አስታውሱን ያልናቸው ሲረሱን</u>

በምድራዊ ሕይወታችን ስኬት ለማግኘት ለብቻችን መሮጥ ውጤት እንደማያመጣ ስናስብ የሚያስብልን የሚያስታውሰን ሰው እንፈልጋለን። ጤንነታችን ተዛብቶ ቀኑ ጨለማ፣ ሜዳው ገደል ሲሆንብን በህክምናው ዘርፍ ይረዱናል ከጐናችን ይቆማሉ ብለን ጨለማ አቋርጠን መንገድ ተሻግረን አደራ ብለን እናሳስባለን። በተቀጠርነው ቀን ስንሄድ የማያውቁን ያህል አዲስ ሲሆኑብን ንዴታችን የእሳት ያህል ይንቦገቦጋል።

ከጌታው ሚስት ጋር ዝሙት አልፈጽምም በማለቱ ተይዞ ወደ ግዞት ቤት የወረደው ዮሴፍ ለፈርዖን ጠጅ አሳላፊ " ነገር ግን በጐ ነገር በተደረገልህ ጊዜ እኔን አስበኝ ምሕረትንም አድርግልኝ የእኔንም ነገር ለፈርዖን ንገረህ ከዚህ ቤት አውጣኝ እኔን ከዕብራውያን ሀገር ስርቀው አምጥተውኛልና ከዚህም ደግሞ በግዞት ቤት ያኖሩኝ ዘንድ ምንም አላደረግሁም" (ዘፍ. 40፣ 14-16) ብሎት ችግሩን ሁሉ አስረድቶ ነግሮት ነበር።

እኛም መከራ ላይ፣ ችግር ላይ፣ በመሆናችን ያስታውሱናል፣ ያስቡናል ጥሩ ስራ ይዘዋል፣ ጥሩ ደመወዝ ይበላሉ ብለን ይደርሳሉ ያልንበት ቦታ ሲደርሱ ያለመፈጠራችንን ያህል የረሱን ዘመድ ጓደኞቻችን አሉ።

ዮሴፍ ለጠጅ አሳላፊው አስታውሰኝ፣ አስበኝ ብሎ ቢነግረውም " የጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ግን ዮሴፍን አላሰበውም ረሳው እንጂ"





(ዘፍ. 40፣ 23) ።

ያስታውሱናል ያልናቸው ሰዎች ሲረሱን፣ ይረዱናል ያልናቸው ሰዎች እጃቸው ሲያጥርብን ነገረናቸው እንዳልሰሙ እያዩን እንዳላዩ ሲሆኑብን ሰማይ የተደፋብን ያህል ይከብደናል።

አንዳንድ ጊዜ የእኛ ለራስ ማሰብና ለራስ መጨነቅ ብቻ ሙሉ በሙሉ ትልቅ ስኬት የሚያመጣ እየመሰለን ንግግራችን ሰሚ ሲያጣ ያስታውሱናል ያልናቸው ሲረሱን ምክንያቱ የጌታ ዝምታ ነው ያልን አለን።

ተ. <u>መሞት አለባቸው ያልናቸው ሲኖሩ</u>

አንዳንድ ሰዎች ሞትን ያመጣ እግዚአብሔር ነው ሲሉ እናደምጣለን። እንደመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ግን ሞትን በሰው ልጅ ላይ ያመጣው እራሱ ሰው ነው። እግዚአብሔር ለመጀመሪያው ሰው አዳም " ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" (ዘፍ. 2፣ 16-17) ብሎታል።

ይህ ማለት ከበላህ ትሞታለህ ካልበላህ ትኖራለህ አትሞትም ማለት ነው። ሰው ቢበላ የመሞት ባይበላ ያለመሞት መብት ነበረው ስለዚህ የመብላት ነፃነቱን ተጠቅሞ በላ ከዚያም ሞት ተወለደ እንጂ እግዚአብሔር ሰው ይሞት ዘንድ ለሞት አልፈጠረውም።

እንኳን የሰዎችን የራሳችንንም ሕይወት ለወሰንበት ውሳኔ



www.ethiopianorthodox.org

ማብቃት ምን ያህል ከባድ መሆኑን ህይወት ራሷ ታስተምረናለች።

ሰውን እንኳን ልንፈጥር፤ በመፈጠራቸው ጉዳይ ከእግዚአብሔር ጋር ውይይት የሌለን ሰዎች በሞታቸው ጉዳይ ገብተን ስንወስንና ስናፈርስ እንገኛለን።

እንደእኛ ሀሳብ የማታውን ባናውቅም የቀን ውሎአቸውን አይተን፣ የነገውን ማንነታቸውን ባናውቅም ዛሬ ያየነውን አይተን የልባቸውን ሀሳብ ሳናውቅ የንግግራቸውን ጥፍጥና ተመልክተን ከየት እንዳመጡት ሳናይ የመጸወቱትን ብር አይተን መሞት የለባቸውም ብለን እንወስናለን።

የፀዳና የዘመኑን ምርጥ ልብስ መልበሳቸውን፣ ዋጋው በሰው የተደነቀ ሽቶ መሹማታቸውን፣ አድናቆት የተቸረው መኪና መያዛቸውን አይተን እንኳን ሲሞቱ፤ ሲታመሙ እንዴት? የምንላቸው አለን።

እናት ወልዳ በሞት የተለየቻቸው፣ ወልዳ ለመከራ የጣለቻቸው የወንድና የሴትን ልዩነት ያልለዩትን ህፃናት በየመንገዱ የእታላዮች ሲሳይ ሲሆኑ መሞት ያልተመኘንላቸው እንገኝ ይሆን?

የወላጆች አለመስማማት፣ የአባትና እናት በሞት መለየት፣ የመጥፎ ሱስ ተገዥ በመሆን ቤት እያላቸው ላስቲክ ዘርግተው የሚያድሩ፣ ንጽህ ምግብ እያለ እኛ አይበላም ቆሻሻ ነው ተበላሽቷል ብለን ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ የጣልነውን ቆሻሻውን እየገለባበጡ ሲበሉ እናያለን።





ያም አላጠግባቸው ብሎ በየታክሲውና አውቶቡስ ፌርማታ አምስትና አስር ሳንቲም ሲለምኑ ቢሞቱ ምናለ ብለን የወሰንን ስንቶች ነን?

በዘመድ በወገኖቻቸው ተደፍረው ለአካል መጉደል ለአእምሮ ህመም ተዳርገው በደላላና በአጭበርባሪዎች ተታለው ኑሮ ከብዶባቸው ዛሬን ለመኖር ነገ ላይ ቆመው አካላቸውን ለመሸጥ ሆዳቸውን ለመሙላት በር ላይ ቆመው በብርድና በሰካራም ስድብ ይንገላታሉ። እኛም ችግራቸው ሳይገባን ያሳለፉት ስቃይ ሳይታየን ሴተኛ አዳሪዎች በማለት ረድተን ለረጂዎች መስጠት ሲገባን ስድበን ለሰዳቢዎች በመስጠት የመጣው በሽታ እንዲጨርሳቸው ሞት አልተመኘንም?

ማንነታቸውን ከእነርሱ በላይ ሳናውቅ ኃጢአተኛ፣ ሌባ፣ ውሸታም ተብለው የሰማነው ሁሉ ላይ ሞት ስንመኝ ጻድቅ፣ ቅን፣ ቸር ተብለው ሀገር ያጨበጨበላቸውን ሰዎች አይተን ማንነታቸውን ሳናውቅ መኖራቸውን የተመኘንላቸው የሉም ይሆን?

ስለእኛ ከእኛ በላይ ብቻ ሳይሆን ከእኛ እኩል የሚያውቅ እንደሌለ ሁሉ ስለሰዎችም ከእነርሱ በላይ እኛም ሆንን ማንም ሰው አያውቅም።

ከዚህም ሌላ በህይወታችን መከራ ያደረሱብንን በሰዎችም ህይወት ግፍ ፈፀሙ ያልናቸውን ሰዎች ስናይ መሞት አለባቸው ግን ለምን ይኖራሉ? እግዚአብሔርስ ፍርዱ ወደየት አለ? ለምንስ ይህ ሲደረግ እያየ ዝም ይላል? እንላለን።



www.ethiopianorthodox.org

### ቸ. <u>የተፈጥሮ አደጋዎች ሲያውኩን</u>

ነቢዩ እግዚአብሔር ኤልያስ በአክአብና ኤልዛቤል ስደት ስለደረሰበት ለመንገድ የሚሆነውን ምግብ እና ውኃ ከተመገበ በኋላ እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና ሌሊት ሄደ።

ከዚያም ዋሻ ውስጥ አደረ። እዚህ ምን ታደርጋለህ? ተራራ ላይ ውጣ የሚል ቃል ወደእርሱ ስለመጣ እርሱም ወጣና ቆመ። እነሆም እግዚአብሔር አለፈ። በእግዚአብሔርም ፊት ትልቅና ብርቱ ነፋስ ተራሮቹን ሰነጠቀ ዓለቶቹንም ሰባበረ። እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም። (1ኛ ነገ. 19፣ 11)

በዓለማችን ላይ ከሚከሰቱት የተፈጥሮ አደጋዎች አንዱ አውሎ ነፋስ ነው። ይህ ነፋስ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ወቅት በመምጣት ሰውን ይገድላል፣ ቤት ያፈርሳል፣ መንገድ ያበላሻል፣ ከተማ ያወድማል፣ የመብራት ሽቦዎችን ይበጣጥሳል። በዓለማችንም እስከዛሬ በአጥፊነታቸው የታወቁ የዓመቱ የክፍለዘመኑ ከባድና ታላቅ ነፋሳት በመባል ያወደሙትን ንብረትና የነፋሳቱን ስም እናደምጣለን።

ነፋሳቱ ባደረሱት ጥፋት አብዛኛው የዓለማችን ህዝብ ያዝናል። የመከራውን ገፈት የቀመሰን ሰዎችና የጥፋቱ አምጪ እግዚአብሔር የመሰለን ሰዎች እግዚአብሔር ለምን እንዲህ ያደርጋል? ባያደርግስ ለምን ዝም ይላል? እንላለን። ከላይ በጠቀስነው ምዕራፍና ቁጥር ላይ እንደተገለጸው ተራሮቹን የሰነጠቀና አለቶቹን የሰባበረ ንፋስ መጥቶ እንደነበር ገልጾልናል። የሚገርመውና የሚደንቀው ነገር "





እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም" የሚለው ቃል ነው። ይህ ጥቅስ የጥፋቱ ምንጭ እግዚአብሔር አለመሆኑን ያስረዳናል።

ከተፈጥሮ አደጋዎች አንዱ የምድር መናወጥ ነው። ይህም አደጋ ቢሆን ቀላል የማይባሉ ሰዎችን ከመግደሉም በላይ ርጠው የማይመልጡት አስፈሪ አደጋ ነው። እስከዛሬ ዓለማችን ከባድ የተባሉ የምድር መናወጥና የመሬት መንሸራተት አደጋዎችን በተለያዩ ሀገራት አስተናግዳለች። በቅርቡም በሀገራችን የተከሰተውን መሬት መናወጥ አንረሳውም። በ (1ኛ ነገ. 19፣ 11) ላይ " ከነፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም" ይላል።

እሳተ ገሞራም የሰው ልጆችን ሕይወት ከሚያጠፉ አደጋዎች አንዱ ነው። ካለንበት ምድር በታች እሳት፣ ነፋስና ውሀ ያሉ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ከምድር በታች ያለው እሳት ድንገት ፈልቶ ሲገነፍል የሚያደርሰው ጉዳት በቃላት ከመግለጽ በላይ ነው። " ከምድር መናወጥ በኋላ እሳት ሆነ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም" (1ኛ ነገ. 19፣ 12)

እነዚህን የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች በዓለማችን እየመጡ ሕይወትን ወደ ሞት፣ መኖርን ወደ አለመኖር፣ ጣቅን ወደ ለቅሶ፣ ደስታን ወደሀዘን ያስለውጡናል። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለምን እንዲህ ያደርጋል? እሱ ካልሆነስ ለምን ዝም ይላል? እንላለን።

እስኪ እናስብ በምድር መናወጥ፣ በአውሎነፋስና፣



www.ethiopianorthodox.org

በእሳተ-ገሞራ ህጻናት እንዲፈጁ፣ አረጋውያን ሜዳ እንዲወድቁ፣ ወላጆች እንዲንገላቱ፣ ወጣቶች የመኖርን ትርጉም ሳያውቁ፣ ሰዎች በተኙበት እሳት እንዲፈጃቸው እግዚአብሔር ያደርጋል ብለን እናስባለን? ይህን ያህልስ ይጨክናል ብለን እናምናለን?

ታዲያ ማን አደረገው? እንል ይሆናል። እግዚአብሔር ሥራውን የሚሰራበት ጊዜ እንተውለት። ምክንያቱን ለእግዚአብሔር እንተወው።

ነ. <u>መኖር አለባቸው ያልናቸው ሲሞቱ</u>

መኖር ለሁላችንም ትርጉሙ ይለያይ እንጂ በምድር ላይ እስከኖርን ድረስ ውሎ ማደር መሽቶ መንጋቱ አይቀርም ለሰዎች ያለን የመኖራቸው ፍላጎት ከቤታችን ነው የሚጀምረው። በመከራ፣ በጭንቅ፣ በችግር ብቻ ሳይሆን በናፍቆትም ጭምር የወለድናቸውን ሕጻናት ከአፋችን ነጥቀን በማብላት ከልብሳችን ቀደን የማልበስ ያህል ለፍተን ስጋችንን በጭቀን የመመገብ ያህል ተንከባክበን አንድ ሁለት እያልን ዕድሜአቸውን እንቆጥራለን። ሳናስበው የመጣው ሞት ሕይወት ያላቸውን ሕጻናት የታቀፍንበት እጃችንን እስከሬን ያሳቅፈናል።

" እርሱም ገና ሲናገር ሌላ መጥቶ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ በታላቅ ወንድማቸው ቤት ይበሉና የወይን ጠጅ ይጠጡ ነበር እነሆም አውሎ ነፋስ ከምድረ በዳ መጥቶ የቤቱን አራቱን ማዕዘን መታው በብላቴኖቹም ላይ ወደቀ (መጽ. ኢዮብ 1፣ 18)። የኢዮብ ልጆች





እንደሞቱ፡ መኖር አለባቸው ያልናቸውን ልጆቻችንን ሞት ይወስዳቸዋል።

ሕጻንነትን አልፈው የአይናችን ማረፊያ የሆኑ ነገ ይጠሩናል ብለን መግቢያ መውጫቸውን እያየን ገብተው እስክናያቸው ወጥተው እስኪመለሱ ሞታቸው የማይታወሰን መኖራቸው ብቻ የሚታየን ወጣቶች በየጐጆአችን ነበሩ። ዛሬ ግን በአንድም በሌላም ምክንያት ከቤታችን አጥተናቸው ሞት ወስዶብን ስማቸው ሲነሳ ፎቶአቸውን ስናይ በአካል የመጡ ያህል እንጆታችን የሚላወስ ብዙዎች ነን።

በጋብቻ ውስጥ ለመኖር ወስነን ወደጋብቻ ያመራን ሰዎች ከትዳር አጋሮቻችን ጋር አብረን ለመኖር የማንወጣው ዳገት የማንሸከመው መከራ የለም። መከራውን አብረን አልፈን ልጆች ወልደን ብዛታቸውን ወስነን፣ የምንኖርበት ቤት፣ ልጆቻችንን እንዴት እንደምናሳድግ፣ የትዳር አጋሮቻችንን እንዴት እንደምናፈቅር፣ እንዴት እንደምንታዘዝ እናልማለን።

አብረን የምንዝናናበት ቦታ፣ የምንመካከረው ምክር፣ ታይቶን ወዳሰብነው ትዳር ከገባን በኋላ ግን የወደድናቸውን ያፈቀርናቸውን የትዳር አጋሮቻችንን ሞት የወሰደብን አለን። በዚህም ምክንያት ብርቱ የነበርነው ደክመን፣ ተስፋ የነበረን ተስፋ ቆርጠን፣ አካል የነበረን አካላችን ጐድሎ ትዳራችን ያለፈ ታሪክ የሆነብን ጥቂት አንባልም። " ኢየሱስም ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ አምስት ባሎች ነበሩሽና" (ዮሐ. 4፣ 17) የሰማርያይቱ ሴት ትዳር የነበራት



www.ethiopianorthodox.org

ብትሆንም በወቅቱ ግን በምን ዓይነት ሕይወት ውስጥ እንደነበረችና ያንን ሕይወቷን ለመለወጥ ጌታ ወደ እርሷ እንደመጣ ይህ ጥቅስ ያስረዳናል።

ወደማህበራዊው ሕይወትም ስንጓዝ በምንሰራበት ቦታ ወይም በመንደራችን የተራበ ሲያበሉ፣ የተጠማ ሲያጠጡ፣ የተቸረገ ሲረዱ የምናያቸው ሰዎች አሉ። ንግግራቸው ጥሩ የሆነ፣ የተጣላ የሚያስታርቁ፣ ለሌላው ጥቅም የሚኖሩ፣ የሰውን ጉዳት ማየት የማይወዱ ሰዎች አይሞቱም መሞትም የለባቸውም ብለን እንናገራለን።

የሚገርመው ግን መሸቶ ሲነጋ የነዚህን ሰዎች መኖር ሳይሆን መሞት እንሰማለን። አንድ ቀን ሰው ለመቅበር ወደ መቃብር ስፍራ ስንገባ መሞታቸውን ያልሰማናቸውን ሰዎች መቃብራቸውን አይተን ለምንድነው እግዚአብሔር መኖር ያለባቸው ሰዎች ሲሞቱ ዝም የሚለው? በማለት በውስጣችን ያለውን ንዴት በእግዚአብሔር ዝምታ ላይ እንናገረዋለን።

### ምዕራፍ ስምንት

<u>ዝምታው እስከ መቼ?</u>

ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ የበላይ ሆነን የተፈጠርነው ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ዝምታ ይታይብናል። ከሰዎች ጋር በሚኖሩን የተለያዩ ግጭቶች የምንሳደብ፣ የምንማታ፣ የምንደባደብ ከዚያም በላይ ለውሳኔ





የምንዳረግ ሰዎች ብንኖርም አንዳንዴ ግን ዝም እንላለን። ለምን? ብንል የምንፈልገውን ማድረግ የምንችልበት አቅም አጥተን ይሆናል፣ የተመቻቸ ቦታ ስንፈልግ ይሆናል ካልሆነም እስኪ ሁለተኛ ይድገሙና እንተያያለን ብለን አሊያም በሌላ ምክንያት ይሆናል።

እግዚአብሔር ግን ለምን ይሆን ዝም አለ በምንላቸው ጉዳዮች ዝም ያለው፣

ሀ. <u>እግዚአብሔርነቱን እስከናውቅ</u>

" ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል" (ሆሴ. 4፣6) ይላልና እግዚአብሔር ሕዝቦቹ ካለማወቅ ጨለማ ወደማወቅ ብርሃን ይመጡ ዘንድ ይፈልጋል።

ከእኛ ከራሳችን ሕይወት ጀምሮ ቤታችን ሀገራችንና ዓለማችን ውስጥ የሚደረጉትን ነገሮች ሁሉ እናያለን። ሁሉንም ነገር ማድረግ የሚችሉ ሰዎች ብቻ ይመስሉናል። በዚህም ምክንያት ለእግዚአብሔር በልባችን ስፍራ ሳንሰጠው ለጥበበኞችና ለፈላስፎች ለዚህ አለምም ብልጽግና ብቻ ቦታ ሰጥተን እንኖራለን።

እግዚአብሔር ዝም ይልና በልባችን ሥፍራ የሰጠናቸው ነገሮች የሆነ ስፍራ ላይ ሲቆሙ እናያለን። ከዚያም የእግዚአብሔርን ቦታ የያዙትን ነገሮች አንድ በአንድ ከስፍራቸው አስለቅቀን ለእግዚአብሔር ሥፍራውን እናስረክባለን። እስከዚህ እግዚአብሔር ዝም ይላል።



www.ethiopianorthodox.org

እጅ ካለን ሠርተን ለመኖር በቂ መሆኑን፣ ሥራ ካለን ውሎ ለመግባት በቂ መሆኑን፣ ቤት ካለን አድሮ ለመነሳት በቂ መሆኑን፣ አልጋ ካለን ተኝቶ እንቅልፍን ለማጣጣም እንደሚበቃን ወስነን እግዚአብሔርን እንረሳዋለን።

ዝምታው ከመሬት ዙሪያ የሰፋ እግዚአብሔር ግን የተመካንበት እጅ በደዌ እስኪያዝ፣ ቤት ብንሰራም እስከማንኖርበት፣ አልጋ ላይ ብንወጣም መተኛት እስከማንችል፣ ዝም ይላል።

ያለ እግዚአብሔር ሰላም ያለው ቤት፣ እንቅልፍ ያለው መኝታ፣ እርኪ ውጤት ያለው ልፋት፣ ማግኘት ስለማንችል ይህንን እስክናውቅ እንደማያይ ዝም ይላል።

የሶርያ ንጉሥ ሠራዊት አለቃ የነበረው ንዕማን በብሉይ ኪዳን ዘመን የኃጢአት ውጤት በሆነው ለምጽ ተመትቶ ነበር። ከምድረ እስራኤል ተማርካ የሄደችው ብላቴና ግን ወደሀገርዋ ቢሄድ ሊፈወስ እንደሚችል ነገረችው። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን መፈወስ ባለመቻሉ ከነለምጹ ይኖር ነበር። እርሱም ሂዶ የነቢዩ ኤልሳዕን ቃል ሰምቶ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ ካለበት ደዌ ተፈውሷል
(2ኛ ነገ. 5፣ 1-መጨረሻ)። ይህም ሰው ከተፈወሰ በኋላ "እነሆ ከእስራኤል ዘንድ በቀር በምድር ሁሉ አምላክ እንደሌለ አወቅሁ" (ቁ. 15)በማለት ከእግዚአብሔር ሌላ በምድር ላይ ሌላ አምላክ እንደሌለ መሰከረ።

እግዚአብሔር ከነበሽታው ያቆየው እግዚአብሔርን አውቆት





ከእርሱም ሌላ አምላክ እንደሌለ እስኪያውቅ ነው። ዛሬም ብዙዎቻችን ስለእግዚአብሔር እናውቃለን እንጂ እግዚአብሔርን እናውቀውም። ስለ አበበ ማወቅና አበበን ማወቅ ልዩነት አለው ስለአበበ ከማወቅ በላይ አበበን ማወቅ ይበልጣል።

ስለእግዚአብሔር አውቀናል። በሕይወታችን ውስጥ ደርሶ፣ ሰርቶ ስናየው ግን እግዚአብሔርን አወቅነው ማለት ነው።

ስለዚህ እርሱን ስናውቀው እንኳን በዝምታው ልናዝን የዝምታው አወዳሾች እንሆናለን።

## ለ. <u>የግፈኞች ጽዋ እስኪሞላ</u>

በዓለማችን የምንኖር ማንኛችንም ሰዎች የምንሠራው ስራ በተለይም ደግሞ ግፍን የምንሰራ ሰዎች በስራን ቁጥር ግፋችን ጽዋችንን እየሞላው እንደሚሄድ ልብ ልንለው ይገባል። "ወጥመድ ኃጥአን ላይ ያዘንባል እሳትና ዲን አውሎ ነፋስም የጽዋቸው እድል ፈንታ ነው" (መዝ. 10፣6) በማለት የግፍ ጽዋችንን ውጤት ይገልጸዋል።

የእስራኤል ዘሥጋ የግብጽ ኑሮ እጅግ ከባድ ነበር። ነጻነት በማጣት፣ በግርፋት፣ ሥቃይ በማስከት ብቻ ሳይሆን የተወለዱ ህፃናትን ከሥቃይ ጋር በማስከት የመከራቸው ዘመን በረዘመ ቁጥር የፈርዖን የኃጢአት ጽዋ እየሞላ ነበር።

ለአራት መቶ ሰላሳ ዘመን በመከራ የኖሩ እስራኤላውያን



www.ethiopianorthodox.org

የኤርትራን ባሕር ሲሻገሩ የፈርዖን ጽዋ ግን ሞልቶ ነበር። ጽዋችን ሲሞላ በዘራነው ልክ እናጭዳለን። "በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል። በበረከትም የሚዘራ በበረከት ያጭዳል" (2ኛ ቆሮ. 9፤6) ግፍን የዘራው ፈርዖን ጽዋው ሲሞላ መከራን አጨደ።

ዛሬ ብዙዎቻችን መከራን፣ ችግርን፣ ሰላም ማጣታችንን፣ ረሀብን፣ በሽታን በማየት ምሬታችን ከቤት አልፎ ጎዳና ከሀገር አልፎ አለምአቀፍ ዜና ሆኗል። እስኪ በሌሎች ከማመካኘት ራሳችንን ለተወሰነ ደቂቃ ወዳጠፋነው ጥፋት ተመልሰን እናስብ።

ወልደን የካድን፣ ወልደን የጣልን፣ አስገድደን የደፈርን፣ ትዳር ያፈረስን፣ ነፍስ ያጠፋን፣ በውሸት ያደባደብን፣ በነገር ያጋደልን፣ አደራ የበላን፣ በሐሰት ሰነድ የሰው ቤት ሸጠን ቤተሰብ የበተንን የለንም ይሆን? እስኪ ተመልከቱት ከላይ ከተዘረዘሩት መካከል ቢያንስ በአንዱ ያልተሳተፍን የለንም። እግዚአብሔር ባይዘገይ ኖሮ የእኛ ግፍ የት ያደርሰን ይሆን?

ዘርተን መሰብሰብ ወልደን መሳም ያቃተን፣ ጸሎታችን መልስ ጾማችን ውጤት ያጣው፣ ስብከታችን ሰው መለወጥ ዝማሬአችን ሰው መመሰጥ ያልቻለው የግፍ ጽዋችን ሞልቶስ እንደሆነ?

"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ" (ራእ. 22፤12) ጽዋችን ሞልቶ ሳይፈስ ለይቅርታ እንዘጋጅ። እርሱም ይታረቀን።

አሜን





ሐ. <u>ጠላቶቻችን ወዳጆቻችን እስኪሆኑ</u>

ነቢዩ ዳንኤል ወደተራቡት አንበሶች ጉድጓድ ሲጨመር ለመጨመሩ ምክንያት የሆኑ ሰዎች ነበሩ። መጀመሪያ ነገር ሠርተው ኋላም ወደ አምላኩ እንዳይፀልይ አሳውጀው ወደ አንበሶች ጉድጓድ ተጨመረ።

አንበሶች የሰው ልጆችን ሊጎዱና ሊያጠፉ ከሚችሉ እንስሳት በዋናነት ከሚጠቀሱት ናቸው። ያውም አንበሶቹ ተርበው ነበር። የዳንኤል ወደ ጉድጓዱ መግባት የእርሱን ሕይወት ወደሞት አልቀየረውም። ለዳንኤል ውድቀትና ሞት ሲጣደፉ የነበሩት ሰዎች ነገር ሲሰሩ እግዚአብሔር ዝም ብሎ ነበር። ዳንኤል አንበሶቹ ጉድጓድ ሲገባ ግን የሰው ልጆች ጠላት የተባሉት አንበሶች ከእግዚአብሔር ወደሰው በሚላኩት በቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት ወደ ወዳጅነት ተለወጡ። (ዳን. 6፤ 1-መጨረሻ)

እግዚአብሔርን አዳኝ መጽሐፍ ቅዱስንም ድንቅ ካስባሉት ታሪኮች አንዱ አንበሳና ሰው ከጠላትነት ወደ ወዳጅነት የተለወጡበት ታሪክ ነው።

ብዙውን ጊዜ ውድቀታችንን፣ ሞታችንን፣ ጥፋታችንን የሚመኙ ሰዎች የሚያደርጉትን ጉዞ በሙሉ እግዚአብሔር እያየ ዝም የሚለው እንደ አህዛብ ጣኦታት የማይመለከት ሆኖ ሳይሆን ጠላቶቻችንንም ወዶጆቻችን ማድረግ ስለሚችል ነው።

በእኛ የሩጫ ሀሳብና የእቅድ ክንውን በዓመታት ለውጥ



www.ethiopianorthodox.org

ያላመጣነውን ነገር በእግዚአብሔር ዝምታ ሞት ሕይወት፣ ውድቀት ትንሣኤ፣ ጨለማ ብርሃን፣ ማታ ጠዋት፣ መታሠር መፈታት፣ ፍርሃት ድፍረት፣ ማጣት ማግኘት፣ መታገስ ውጤታማ ያደርጋል።

ሰው ፈጥኖ ወዳጅን ጠላት ቢያደርግም፤ እግዚአብሔር ግን ዘግይቶም ጠላቶቻችንን ወዳጆቻችን ማድረግ ይችላል።

አሜን ያድረግልን።

## መ. እርሱ ለልጆቹ እስኪዋጋ

በሞቱ ሕይወትን የሰጠውን ጌታ የሚያመልክ ክርስቲያን በደስታውም ሆነ በሀዘኑ በማግኘቱም ሆነ በማጣቱ ከእግዚአብሔር ጋር ሊሆን ይገባዋል። እስራኤላውያን ባህረ ኤርትራ ከፊት ለፊታቸው ተንጣሎ ጠላት ከኋላቸው ሲመጣ "በግብፅ መቃብር ስላልኖረ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ አወጣኸንን? ከግብፅ ታወጣን ዘንድ ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው? በምድረ በዳ ከምንሞት ብንገዛላቸው ይሻላልና ተወን ለግብፃውያን እንገዛ ብለን በግብፅ ሳለን ያልንህ ቃል ይህ አይደለምን? አሉት። ሙሴም ለሕዝቡ "አትፍሩ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ። እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል እናንተም ዝም ትላላችሁ አላቸው"

(ዘፀ. 14፣11-15) በበሽታ፣ በረሀብ፣ በድህነት ስንንገላታ የሰው ልጆችን ጠላቶች ድል እንዲያደርግልን የእርሱን ማዳን ተስፋ





በማድረግ እኛ ዝም ማለት አለብን::

እግዚአብሔር ሲዋጋ ባሕር ይከፍላል፣ የጠላትን ፍላጻ ያስወጡት ይጨርሳል፣ የጠላትን አስክሬን ባሕር ላይ ያንሳፍፋል:: ረሀብን ሲዋጋ መና ያወርዳል፣ ጥማትን ሲዋጋ ውኃ ያፈልቃል፣ የፀሐይን ቃጠሎ ሲዋጋ ደመና ይጋርዳል፣ ጨለማን ሲዋጋ ፀሐይ ያቆማል::

## ሠ. ዝም ያለበትን እስክናውቅ

ሰዎች ዝም ያሉበትን ምክንያት ሲናገሩ እናውቃለን:: ካልሆነም እንገምት ይሆናል:: እግዚአብሔር ለምን ዝም እንዳለ የምናውቀው ከዝምታው በኋላ ባየነው ውጤት ነው::

አሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት ከብዙ ባለመድድኒቶች ብዙ ስትሰቃይ ገንዘብዋንም ሁሉ ከስራ ሲብስባት የጌታን ፈዋሽነት ሰምታ ወደ እርሱ እስክትመጣ ዝም ያላት ለካ ኃይል ከእርሱ ወጥቶ ልብሱን ዳስሳ እስክትፈወስ ነበር:: (ማር. 5÷25-34) ከነናዊቷ ሴት ስለልጇ በጌታ እግር አጠገብ ስትጮህ ዝም ያላት የደቀመዛሙርቱ አማላጅነት እንዲገለጽና የእርስዋ ትዕግስት የሃይማኖት ጽናትና ትህትና እንዲታወቅ ፈልጎ ኖሯል:: (ማቴ 15÷21-29)

ጌታ የ38 ዓመቱን በሽተኛ ሰው አጥቶ፣ ከአልጋ ተጣብቆ ሲኖር 38 ዓመት ሙሉ ዝም ያለው የ38 ዓመት በሽተኛ እንኳን መፈወስ የሚችልና የህመምተኞች ሰብሁ ዘመናት አልጋ ላይ መተኛት ለእርሱ ምንም አለመሆኑ ለማሳየትም ነበር:: (ዮሐ 5÷1-18)



www.ethiopianorthodox.org

## የእግዚአብሔር ዝምታ እስከመቼ

ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ ሕጋችንን አፍርሷል፣ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓል፣ ሰንበትን ሽሯል፣ ሲሉት ዝም ያለው ለካ የእርሱ መሞት ለሚሰቅሉት ለእነርሱም አስፈላጊ ስለነበር ነው:: (ማቴ 26÷62)

የንጉሡ አርጤክስስ ባለሟል ሐማ መርዶክዮስንና እስራኤላውያንን ለማጥፋት ሲያሴርና ለመርዶክዮስ መስቀያ 50 ክንድ ግንድ እስኪያዘጋጅ ዝም ያለው ሐማ ባዘጋጀው ግንድ ላይ ራሱ እስኪሰቀል ነበር:: (አስ.3÷7)

በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መሠረት እግዚአብሔር ዝም ያለበትን የምናውቀው ከዝምታው በኋላ ነው::

«እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ወደ ፍርድ ያመጣዋልና» (መጽ. መክ. 12÷14)


## ዋቢ መጻሕፍት

1. መጽሐፍ ቅዱስ በ1962 ዓ.ም. የታተመ
2. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በ1989 ዓ.ም የታተመ
3. መጻሕፍተ ሐዲሳተ ሠለስቱ በ1989 ዓ.ም የታተመ
4. ጉዞ ወደ እግዚአብሔር በ1989 ዓ.ም የታተመ
5. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ በ1974 ዓ.ም የታተመ::




www.ethiopianorthodox.org